## „ህግን የሚጥስ መንግስት የወንበዴዎች መንግስት ከመባል አያልፍም“ !

### -ፓፕ ቤኔዲክት 16ኛ የጀርመን ፓርላሜንት ውስጥ  ያደረጉት ንግግር-

ፖፕ ቤኔዲክት 16ኛ ጀርመንን እ.አ በ22.09.2011 በጎበኙበት ወቅት በፓርላሜንት ውስጥ ያደረጉት ንግግር ለማንኛውም አገር አገዛዝ ትምህርት ሊሆን ይችላል ብዬ ስላመንኩ በጋዜጣ የቀረበውን የተወሰነ ክፍል እንዳለ ተርጉሜ ለአንባብያን አቅርቤዋለሁ።

„ህግን እንዳለ አንስተህ መንግስት ካለህግ አገር እንዲገዛ ካደርግህ ወይም ራሱ በመሰለው ህግ እገዛለሁ የሚል ከሆነ ፣ ቅዱስ አውግስቲኑስ እንደሚለው እንደዚህ ዐይነቱ መንግስት የወንበዴዎች ወይም የዘራፊዎች መንግስት ተብሎ ከመጠራት ሌላ ስም ሊሰጠው አይገባም።  በተለይም እኛ ጀርመኖች እንደዚህ ዐይነቱ አባባል የሚያስፈራ ባዶ አነጋገር አለመሆኑን ከታሪካችን ልምድ በደንብ እናውቀዋለን። በደንብ እንደምናውቀውና እንደኖርንበትም ፣ ስልጣን ከህግ በመነጠሉና መንግስትም ህግን አውዳሚ እንዲሆን ወደ መሳሪያነት በመለወጡ የተነሳ ይህ ነው የማይባል ግፍ እንዳደረሰ እናውቃለን።

ከዚህ ዕምነት በመነሳት ፣ የሂትለርን የናዚ አገዛዝና ፣ እንዲሁም ሌሎች አምባገነናዊ አገዛዝን አጥብቀው የተቃወሙና የተዋጉ ኃይሎች ለጀርመን ህዝብ ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም የዓለም ህዝብ ለነጻነቱ በሚያደርገው ትግል ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳበረከቱ የማይታበል ሀቅ ነው። በጊዜው የናዚን አገዛዝ አጥብቀው ይቃወሙና ይዋጉ የነበሩ ኃይሎች በነሱ ዕምነት በናዚ አገዛዝ ዘመን ተግባራዊ የነበረው ህግ በራሱ የሰውን ልጅ መብት የሚጻረር ስለነበር በፍጹም ተቀባይነት የነበረው ህግ እንዳልነበር በመገንዘብ ነው። ከዚህ በመነሳት አንድ በዲሞክራሲያዊ መርሆች ደንብ መሰረት የተመረጠና ህዝብን የሚያገለግል ፖለቲከኛ አንድ ውሳኔ ላይ ከመድረሱ በፊት ትክክል ነው ብሎ የሚያምንበትን ፣ እኩልነትን ለማስፈኑም ሆነ ይህ ደግሞ ወደ ህግ ሲመነዘር አድልዎ ያስከትል አያስከትል እንደሆነ አፍን ሞልቶ ለመናገር በጣም ያዳግታል። ስለሆነም አንድን ህግ በዕውነተኛ የሳይንስ መነጽር ለመመርመርና እኩልነትንም ያሰፍን እንደሆን ለማወቅና ፣ ይህንንም ህጋዊ ለማድረግ በቀላሉ የሚመለስ ነገር አይደለም። በተለይም የተለያየ ዕውቀትና ኢንፎርሜሽን በተትረፈረፈበትና ሀቁን ከውሸት ለመለየት በሚያስቸግርበት በአሁኑ ዘመን አንድን ወደ ህግ የተለወጠን ነገር የእኩልነት መመዘኛ አድርጎ ለመቀበል በጣም እያስቸገረ መጥቷል።

አሁን ባለንበት ፣ በተለይም ተቀባይነትን ያገኘና አርቆ አሳቢነትን ያጠለቀ የሚመስል ሳይንስና (Positive Science) ፣ ይህም የሰውን ልጅ ዕድል ወሳኛና አማራጭ የሌለውና ብቸኛው ተደርጎ በተወሰደበት ዘመን ሌሎች ለሰው ልጅ ጠቃሚ የሆኑ ደንቦችና ባህሎች እየተረገጡና እንደ ዝቅተኛና አላስፈላጊ ሆነው በመምጣታቸው የሰውን ልጅ ከፍተኛ አደጋ ውስጥ እየከተቱት ነው። ስለሆነም በአለንበት ዘመን በሳይንስ ስም የሚካሄደው ነገር ሁሉ የሰውን ልጅ እያሳነሱትና ከሰብአዊነት ባህርይው እንዲርቅና እየተፈራራ እንዲኖር እያደረጉት በመምጣት ላይ ናቸው። ይህንንም የምናገረው አሁን አውሮፓ የሚገኝብትን ሁኔታ በመመልከትና ፣ ይህ ፖዘቲቭ ሳይንስ እየተስፋፋ በመምጣቱ ሌሎች ለሰው ልጅ የሚጠቅሙ የአኗኗር ስልቶችንና ባህሎችን እንደ አልባሌና እንደ ህገ-ቢስ ተደርጎ በመወሰዱ ይህ ሁኔታና ተቀባይነትን ያገኘ የመጣው አንድ ወጥ አመለካከት ስላስፈራኝ ነው። በመሆኑም ይህ አውሮፓ ውስጥ ተቀባይነትን ያገኘና በሰዎች ትከሻ ላይ የሚጣል ፖዘቲቭ ህግ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነትን እያገኘ በመምጣት በተለያዩ አገሮች ለብዙ መቶ ዐመታት ሰፍነው የነበሩ ጥሩ ባህሎችንና ኖርሞችን እየደመሰሰ በመምጣት ላይ ነው። ይህ ዐይነቱ የበላይነትን ማስፈንና የሌሎችን አገሮች የአሰራር ልምድና ባህል ከቁጥር ውስጥ የማያገባ በብዙ መልኮች የሚገለጸው ፖዘቲቭ ሳይንስ ወይም ህግ በየአገሩ ለአክራሪዎች መነሻ ምክንያት እንደሆነ የማይታበል ሀቅ ነው።

የአውሮፓው ባህል የየሩሳሌሙ ፣ የአቴንና የሮም አንድ ላይ መገናኘትና መጣመር የወለደው ነው ብሎ መናገር ይቻላል። በእግዚአብሔር የሚያምነው የእስራኤል ህዝብ ፣

በአርቆ አስተዋይነትና አሳቢነት ላይ የተመሰረተው የግሪኩ ፍልስፍናና ፣ እንዲሁም ደግሞ የህግን ኖርሞች ባፈለቁት ሮማውያን ፣ እነዚህ አንድ ላይ በመጣመር ለአውሮፓው ባህልና አውርፓ ለሚባለው የመለያ ስም ሊሰጡት ችለዋል። የዛሬው አውሮፓ ከእነዚህ ሶስት አመለካከቶች ውጭ ሊታሰብ በፍጹም አይችልም። ስለሆነም ፣ ይህ ዐይነቱ አመለካከትና ዕምነት በሰዎች ጭንቅላት ውስጥ እንዲቀረጽ በመደረጉና ፣ ከእግዚአብሔርም በፊት ኃላፊነታቸውን እንዲያውቁ በመደረጉ የሰው ልጅ መብት ሁሉ በሌላው ተመሳሳዩ ሊረገጥ እንደማይችልና ፣ ሁሉም ከህግ በፊት እኩል ነው የሚለውን አምኖ እንዲቀበልና ተግባራዊ እንዲያደርግ መሰረት ተጣለለት። በመሆኑም ፣ እንደዚህ ዐይነቱን ከተፈጥሮ ህግ የፈለቀውን ህግ የመከላከልና የሰውን ልጅ እኩልነት በዚህች ምድር ላይ ለማስፈን መታገል የማንኛውም ሰው ተፈጥሮአዊ መብት ነው። ስልጣን ከህግ ተነጥሎ በሚታይበት ዓለምና ፣ ጥቂት ግለሰቦች ህግን ለራሳቸው በሚመች መልክ እያወጡና እየተረጎሙ ተግባራዊ በሚያደርጉበት ዓለም ውስጥ ሰላምና ፍቅር በፍጹም ሊሰፍኑ አይችሉምና። ስልጣን ከውዕነተኛ ህግ ተነጥሎ ከታየ እንደዚህ ዐይነቱ አገዛዝ ዘራፊ አገዛዝ (Predatory State) ተብሎ ከመጠራት በስተቀር ሌላ ስም ሊሰጠው አይገባም።“

ይህ ከላይ የሰፈረው የፖፕ ቤኔዲክት 16ኛ ንግግር ተቆርጦ የቀረበ ቢሆንም ፍሬ ነገሩ እንዳለ ነው። እንደኛ ባለው ህብረተሰብ ውስጥ መንግስትና የመንግስት ተግባር ፣ እንዲሁም በህዝብና በመንግስት መሀከል ያለው ግኑኝነት ከፍልስፍናና ከቲዎሪ አንጻር ተመርምሮ ባልተዋቀረበት አገር ውስጥ የኚህ ሊቀ ጳጳስ ንግግር የወደፊቱ ኢትዮጵያ በምን መርሆችና መሰረተ-ሃሳብ ላይ መገንባት እንዳለባት ልንማረውና ከሰውነታችን ጋር ልናዋህደው የሚገባንን ትምህርት ያስተላልፍልናል።

በመሰረቱ የፖፕ ቤኔዲክት ንግግር በእነ ፕላቶንና አርስቲቶለስ ፍልስፍና ላይ የተመሰረተ ሲሆን ፣ በተለይም የካቶሊክ ሃይማኖት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከስድስተኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ ተቀባይነት እያገኘ ከመጣ ወዲህ በእነ ቄስ አውግስቲኑስ አማካይነት ፍልስፍናን ከሃይማኖት ጋር በማገናኘት ወይም በማስታረቅ አንድ ህዝብ ወይም አንድ አገር በምን መሰረተ-ሃሳቦች ላይ ተመርኩዞ ሰላም ፣ ፍቅርና ስርዓት የሰፈነበት ማህበረ-ሰብ ሊመሰረት ይችላል ብለው የአንድን ህዝብ ዕድል ከብዙ ነገሮች አኳያ በመመልከት ያፈለቁትን ሃሳብ መሰረት ያደረገ ነው። ይህ የስልጣን ጥያቄን ከፍልስፍና ጋር ማቀናጀትና ፣ በአንድ በኩል ስልጣንና ህግን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ህዝብና መንግስት በምን መልክ መዋቀር እንዳለባቸው ሲያመለክት ፣ ማንኛውም በአንድ አገር የሚኖር ገለሰብ እንደ ገለሰብ ተፈጥሮአዊ መብት ቢኖረውም ይህንን መብቱን ተግባራዊ ማደረግ የሚችለው የዚያው ህብረተሰብ አካል መሆንኑና ፣ መብት ብቻ ሳይሆን ሃላፊነትም እንዳለበት የተገነዘበ እንደሆን ብቻ ነው። በተጨማሪም በአንድ አገር ውስጥ መንግስት ከፍተኛውን ቦታ ቢይዝም በመንግስትና በህዝብ መሀከል የሚኖር ግኑኝነት የስምምነት ጉዳይ ሳይሆን መንግስት አንድን ህብረተሰብ የማስተዳደር ኃላፊነት እንዳለበት ሁሉ የሚወስዳቸው ማንኛውም እርምጃዎች ፣ ማለትም ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ህብረተሰብአዊ ፣ ባህላዊና ሌሎች ነገሮች ሁሉ ከጠቅላላው ህብረተሰብ አንጻር ጥቅም የሚነደፉና ተግባራዊ መሆን ያለባቸው ናቸው። በሌላ አነጋገር ፣ በተፈጥሮ ህግና በእነ ፕላቶን ፍልስፍናና ፣ በኋላም በተነሱት የመንግስት ቴውሬቲሺያን ዕምነት መሰረት መንግስት በራሱ ፈቃድ እየተነሳ ምንም እርምጃ መውሰድ የለበትም። በተለይም በታላቁ የሳይንስና የመንግስት ቴዎሬቲሺያን ላይብኒዝ ዕምነት አንድ ህዝብ ለአንድ መንግስት የሚሰጠው ኃላፊነት በሁለት ግለሰቦች መሀከል እንደሚደረገው የንግድ ወይም ሌላ ዐይነት ስምምነት ከዚህ እስከዚህ ዘመን ድረስ መፈጸም አለበት በሚል ለድርድር የሚቀርብ ሳይሆን ፣ መንግስት የሚባለው አካል በተወሰነ የታሪክ ወቅትና ከርዝም ጊዜ የታሪክ ሂደት በኋላ እያደገ የመጣ እንደመሆኑ መጠን አንድን ህብረተሰብ በስነስርዓት ለማስተዳደርና በህብረተሰቡ ውስጥም የማያስፈልግ ግጭት እንዳይፈጠር መከተል ያለበት መሰረተ-ሃሳቦች አሉ። አንደኛ ፣ መንግስት በአንድ አገር ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ዜጋ በመንግስት አማካይነት ፍላጎቱን ፣ ምኞቱን ፣ ፍቅሩን ፣ ችሎታውን ፣ቤተሰብአዊና ህብረተሰብአዊ ኃላፊነቱን የሚያንፀባርቀበትና የሚወጣበት መሳሪያ ነው። ይህ ዐይነቱ መንግስት የዩኒቨርስን የስምምነትና የተፈጥሮን ህግ የተቀበለ መሆን ሲገባው ፣ ተግባሩ ሁሉ ጠቅላላውን ህብረተሰብ መጥቀምና ፣ እያንዳንዱን ግለሰብ ደግሞ

እንደችሎታውና እንደ አስተዋጽዖው በደስታ እንዲኖር ማድረግ ነው። በሌላ አነጋገር የህብረተሰቡን ኑሮ ስቃይ ለመቀነስና ደስታውን በማጎልበት በፍቅርና በስምምነት እንዲኖር በማድረግ ቀንጆ ቀንጆና ዘላቂነት ያላቸውን ከትውልድ ትውልድ ሊተላለፉ የሚችሉ ነገሮችን መስራት አለበት። ሀለተኛ ፣ እርቆ አሳቢነትን(Rationality) ከሞራልና ከስነ-ምግባር ጋር ያዋሃደ መሆን አለበት። ላይብኒዝ እንደሚለው እርቆ አሳቢነት በሌለበት ቦታ ህግና ስርዓትም በፍጹም ሊኖሩ አይችሉም። ሶስተኛ ፣ ይህ ዐይነቱ አመለካከትና ኃላፊነት በህብረተሰብ ውስጥ መሰረት እንዲጥልና እያንዳንዱ ግለሰብም የራሱን ፍላጎትና ጥቅም ከጠቅላላው ህብረተሰብ ጥቅምና ፍላጎት ጋር በማገናኘት ይሰራ ይችል ዘንድ ማስተማር አለበት። ሶስተኛ ፣ አንድ መንግስት በምንም ጊዜና ቦታ ስልጣን ያዘኩኝ ብሎ የራሱን ኃይል በማጠናከርና ራሱን ከህብረተሰቡ በማግለል ወደ ጨቋኝነት መለወጥ የለበትም። በሌላ ወገን ግን አንድ ህብረተሰብ እየተወሳሰበ ሲመጣና አንዳንድ ነገሮች ሲከሰቱ እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ኃይል መጠቀም ቢያስፈልግም የኃይል አጠቃቀም ከማስፍራራት ተሻግሮ መሄድ የለበትም። በማንኛውም ጊዜና ቦታ የስልጣን መለኪያው እርቆ አስተዋይነትና ተቀባይነት ያገኘው በተፍጥሮ ህግ ላይ ተመርኩዞ የወጣው ህገ-መንግስትና ይህን ተገን አድርጎ የሚፈልቀው የመቅጫና የሲቪል ህግ ነው። አራተኛ ፣ እንደዚህ ዐይነቱ መንግስት ፣ የጀርመን ክላሲኮችን አባባል ለመጠቀም ፣ ምንግዜም ቢሆን ጥበባዊ መሆን አለበት። በሌላ አነጋገር በቢሮክራሲያዊ ህግና ስራ ያልተንዛዛና አንድን ህዝብ የማያጉላላ መሆን አለበት። የህዝብን ልብና ስሜት የሚያነብ ፣ ከህዝብ ያልራቀና ህዝብን የማይፈራ ፣ በሚያስፈራሩ ኃይሎች እየተከበበ የማይሄድ መሆን አለበት። አምስተኛ ፣ አንድ መንግስትና አገዛዝ በአንድ አገር ውስጥ ያለን የተፈጥሮን ሀብትና መሬትንም ጨምሮ የራሱ አድርጎ በመቁጠር እንደፈለገው ሊሸጥና ሊለውጥ ፣ ስልጣን ላይ ብቻ ለመቆየት ሲል የተወሰነውን ህብረተሰብ ክፍል በማቅረብ ብቻ ለሱ የተወሰነ ጥቅም በመስጠት ኃይሉን የማጠንከርና የተስተካከለ ዕድገትና እኩልነትን የሚጻረር ድርጊት ማካሄድ የለበትም። በአንድ አገር ውስጥ ያለ የተፈጥሮ ሀብት ምንግዜም ቢሆን የጠቅላላው ህዝብ ሀብት ሲሆን ፣ በዚያ አገር ውስጥ የሚኖር ህዝብ እንደ ችሎታውና እንደሀብቱ የመጠቀምና አገርን በማልማት ሂደት ውስጥ የመሳተፍ መብት አለው። አድልዎ በሰፈነበትና ጥቂቶች ብቻ ተጠቃሚ በሆኑበት ህብረተሰብ ውስጥ ህብረተሰብአዊ ውዝግብ መኖሩ የማይቀር ጉዳይ ነው። ስድስተኛ ፣ አንድ መንግስት የአገሩን ብሔራዊ ነፃነት የማስከበርና ዜጎቹም በውጭ አገር እንዳይናቁ ወይም ተከብረው እንዲኖሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት። ሰባተኛ ፣ በማንኛውም ጊዜና ቦታ አንድ መንግስት የሌላ ውጭ ኃይል ተገዢ ያልሆነና የሌላ መንግስት ተወካይ በመሆን በሌሎች አገሮች እየገባ በመፈትፈት ሰላም አናጊና ጸብ ጫሪ መሆን የለበትም። አንድ መንግስት ሊከበርና ሊፈራ የሚችለው የራሱን የቤት ስራ ሲሰራና ፣ ወድ ውጭ ደግሞ የውክልና ጦርነት የማያካሂድና ሁልጊዜም ለሰላምና ተሳስቦ ለጋራ ዕድገት ለመነሳት የሚችል እንደሆን ብቻ ነው።

ከዚህ ከላይኛው አጠር መጠን ብሎ ከቀረበው ሀተታ በመነሳት ነው አንድ መንግስት ወይም አገዛዝ ተቀባይነት(Legitimation) ይኑረው አይኑረው መምርመር የሚቻለው። በሌላ ወገን ግን በላይብኒዝ ዕምነት በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት መስራት በራሱ እንደ ዋና ዓላማ ሆኖ መወሰድ የለበትም። በሞራል ላይና የታሪክን ኃላፊነትን በተመረኮዘ አሰራር ላይ ተግባራዊ የሚሆን ለአንድ ህብረተሰብ የሚጠቅም ስራ የግዴታ ተቀባይነትን ያስገኛል። ለመመረጥና ስልጣን ላይ ለመቆየት ሲባል ብቻ ደፍ ደፍ የሚባል ነገር ሳይሆን ፣ አንድን ህብረተሰብ በጸና መሰረት ላይ ለመገንባት ሳይንስና ቴክኖሎጂን መሰረት በማድረግ አንድ ህብረተሰብ ለታሪካዊና ለቆንጆ ስራዎች እንዲነሳ ግንዛቤ ውስጥ እንዲኖረው ማድረግ በራሱ የመንግስት ታሪካዊ ኃላፊነት ነው። በተፈጥሮ ህግ ላይ ተመርኩዞ የሚገዛ አገዛዝ ምንጊዜም ቢሆን ህብረተሰብአዊ ኃላፊነት እንዳለበት የሚገነዘብ ሲሆን ፣ ህብረተሰቡ ፍቅር ይለግሰኛል ፣ አገዛዜን ይደግፈዋል ፣ እንደገናም መልሶ ይመርጠኛል ብሎ በመገመት የሚወስዳቸው እርምጃዎች መኖር የለበትም። አንድ አባት ለማንም ሳያደላ ለቤተሰቡ ኃላፊነት እንዳለበት ሁሉ ፣ አንድ መንግስትም በማንኛውም ጊዜና ቦታ ግዴታና ኃላፊነቱ ለጠቅላላው ህዝብ ብቻ ነው።

ይህ በፓፕ ቤኔዲክት 16ኛ በጀርመን ፓርላሜንት ውስጥ የተነበበው ንግግር በጣም ውስን በሆነ መልክ ካልሆነ በስተቀር በምዕራብ አውሮፓ የመንግስትና የአገር አገነባብ ታሪክ ውስጥ ጎልቶ የታየበት ቦታ የለም። በሬናስን አማካይነት ከፍተኛ የሆነ የስልጣኔ እንቅስቃሴ በማካሄድ ለሳይንስ በር ለመክፈት የተቻለ ቢሆንም ፣ ስልጣንን ለመያዝ በሚታገሉ ኃይሎች መሀከል በሚደረገው ሽኩቻ ሙሉ በሙሉ ሰላምንና እኩልነትን ለማስፈን አልተቻለም ነበር። በቤተክርስቲያንና በፊዩዳል አሪስቶክራቶች መሀከል በሚደረገው የብዙ መቶ ዐመታት የማያቋርጥ ግጭት በተፈጥሮ ህግ ላይ የተመሰርተ ህግን ተግባራዊ በማድረግ እኩልነትን ለማስፈን አልተቻለም ነበር። በ17ኛው ክፍለ-ዘመን ደግሞ የህብረ-ብሔር አገዛዝ በአንዳንድ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ሲቋቋም የፍጹም ሞናርኪዎች አትኩሮአቸው ወደ ውስጥ በማኑፋክቱር ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ መገንባት ነበር የጀመሩት። በእነ ፕላቶንና ከዚያም በኋላ በቄስ አውግስቲኑስና ላይብኒዝ ፣ እንዲሁም በቫይማር ክላሲኮች ፣ በእነሺለር የታለመው ጥበባዊ መንግስትን የመመስረቱ ጉዳይ በፍጹም ዕድልን አላገኘም። የኢንዱስትሪ አብዮት ከእንግሊዝ አልፎ በሌሎችም የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ሲቀጣጠል ኢኮኖሚያዊ ኃይልን እየተቀዳጀ የመጣው የከበርቴ መደብ ከኢኮኖሚው የውስጥ-ኃይል ጋር የሚጓዝ ቢሮክራሲያዊ አስተዳደር መመስረት እንዳለበት በመገንዘብ በፍጹም ሞናርኪዎች ላይ ግፊት ማድረግ ጀመረ። ካፒታሊዝም እያደገና እየተስፋፋ ሲመጣ የፊዩዳል አስተዳደር መዋቅሮች በመፈረካከስ አዳዲስ የህብረተሰብ ኃይሎች ተፈጠሩ። በዚያው መጠንም ካፒታሊዝምን ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ዕውቀት በአዲስ መልክ መቀናጀት ነበረበት። በአዲሱ የህብረተሰብ ኃይል አሰላለፍና በካፒታሊዝም በአሸናፊነት መውጣት የተነሳ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትን ያገኘው ፖዘቲቭ ሳይንስ በድል አድራጊነት መውጣት ቻለ። በእንግሊዝ ኤምፔሪሲስቶች የፈለቀው የከበርቴውን የበላይነት የሚያረጋግጥ የህግ የበላይነትና ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ ነጻ ንግድን ማስፋፋትና በምሁርም ሆነ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ወደ ኋላ የቀሩ አገሮችን ዕድል ለመወሰን በአውሮፓ ኃያል መንግስታት መሀከል የጦፈ ውድድር ተጀመረ። ከዚያን ጊዜም ጀምሮ እኩልነትና ህግ የሚሉት ጽንሰ-ሃሳቦች በተለያዩ ኃይሎች የተለያዩ ትርጉም ተሰጣቸው።

ዛሬ እንደምናየው በብዙ የሞዕራብ አውሮፓ አገሮችና አሜሪካንም ጭምር የፓርሊሜንተሪ ዲሞክራሲ ሰፍኗል። በመንግስትና ኢኮኖሚውን በሚያንቀሳቅሱ ኃይሎች መሀከል ግልጽ የሆነ አሰላለፍ አለ። እንዲሁም ህግን በሚያወጣውና ህግን ተግባራዊ በሚያደርገው መሀከል ግልጽ የስራ ክፍፍል አለ። በሌላ አነጋገር መንግስት በህግ አስፈጻሚው ላይ ፖለቲካዊ ግፊት አያደርግም። በተጨማሪም በየጊዜው በምርጫ ተወዳድረው ስልጣን የሚይዙ ፓርቲዎች የህዝብን መብት ለመገደብ የመንግስትን መኪና እንደፈለጉ ሊጠቀሙ አይችሉም። ይሁንና የተለያዩ ምክንያቶችን በመፈለግ ፣ ለምሳሌ የሽበርተኝነትን ጉዳይ አጠንክሮ በማንሳት የጠቅላላው ህዝብ ነፃነት በጥያቄ ውስጥ እስከሚገባ ድረስ በጣም የረቀቁ ህጎችን ያወጣሉ። ለዚህም ደግሞ አሁን ውስብስብ እየሆነ የመጣውን የኮምፑተር ቴክኖሎጂን በመጠቀም የግለሰቦች የደብዳቤ ልውውጥን ማንበብ የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥሮአል። የስልክም ውይይት እንደዚሁ ይጠለፋል። ግለሰቦች እንደዚህ ዐይነቱን የመሰለ የመንግስትን የረቀቀ ክትትል በፍጹም ሊቆጣጠሩ የማይችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል ማለት ነው። ስለሆነም ማንኛውም ዜጋ ከህግ ፊት በፎርማል ደረጃ እኩል ነው ቢባልም እዚያው በዚያውም እኩልነቱንና መብቱን በጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ ብዙ የረቀቁ ቢሮክራሲያዊ የአሰራር ስልቶች ተዘርግተዋል። እኩልነት የሚለውን ጽንሰ-ሃሳብም ጠጋ ብለን ስንመለከት አሻሚ ትርጉም እንዳለው እንረዳለን። ከክርስቲያን የዲሞክራቲክ ፓርቲ እስከ ሊበራልና ሶሻል ዲሞክራቶች ጀምሮ እኩልነት የሚለውን ጽንሰ-ሃሳብ እንደፈለጉት በሚስማማቸው መልክ ይተረጉሙታል። በዚህ መልክ ዜጎች ከህግ ፊት እኩል ናቸው ተብሎ ቢሰበክም ወደ ተጨባጩ ሁኔታ ስንመጣ ኢኮኖሚውን የሚቆጣጠረው በተለይም የኢንዱስትሪና የፊናንስ ካፒታል ፣ እንዲሁም ትላልቅ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በህዝብ የተመረጡትን ተወካዮች ተብትበው በመያዝ ማንኛውም ህግ ለፊናንስና ለኢንዱስትሪ ካፒታል በሚስማማ መልክ እንዲወጣ ከፍተኛ ግፊት ይደረጋል። አልፎ አልፎ የኢኮኖሚ ቀውስም በሚከሰትበት ወቅት የአንጀት አጥብቅ የኢኮኖሚ ፖሊስ ሲወጣ የሀብት ባለቤት ባልሆነው ሰፊ ህዝብ ላይ ነው ፖሊሲው የሚጫነው። ለከበርቴው መደብ ቀረጥ

መቀነስ ፣ የሰራተኛውን መደብ የመደራደር ኃይል ማዳከምና በሞነቴሪ ፖሊሲ መጉዳት የሚያመለክተው የቱን ያህል የፓርሊሜንታሪ ዲሞክራሲ ውስን መሆኑን ነው። ይሁንና በካፒታሊዝም ውስጥ በሚታየው ከፍተኛ የሲቭል እንቅስቃሴ የከብርቴው መደብም እንደፈለገው ሙሉ በሙሉ ተደላድሎ መግዛት የማይችልበት ሁኔታ አለ። የሲቭክ ማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች በየጊዜው እያደጉና በምሁርም ደረጃ በከፍተኛ ደረጃ ተወዳዳሪ እየሆኑ መምጣት በመንግስት መኪና ላይ ጫና እንዲያደርጉ አስችሏቸዋል። የዲሞክራሲውና የእኩልነት ትግሉ በዚህ መልክ ነው የሚካሄደው። ዘለዓለማዊ ፍጥጫ ያለበት!

ከላይ በተጠቀሰው መልክ በምዕራቡ የካፒታሊስት ዓለም በአንድ በኩል መንግስት የጎላና ግልጽ ተግባር ቢኖረውም ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በተለይም ከ1980ዎቹ ወዲህ የፊናንስ ካፒታል እያየለ መምጣት በመንግስት መኪና ላይ ከፍተኛ ጫና ማድረግ የሚያስችለው ርዕዮተ-ዓለማዊ መሰረት ተዘጋጅቶለታል። በፖዘቲቭ ሳይንስ ወይም በኤምፐሪሲዝም ላይ የሚመረኮዘው የኒዎ-ሊበራል ርዕዮተ-ዓለም በየኢንስቲቱሽኖች ውስጥ ሁሉ ሰርጎ በመግባት የበላይነትን ሊቀዳጅ ችሏል። በተለይም የፊናንስ ካፒታል በጣም ተንቀሳቃሽ መሆንና በተለያዩ መልኮች መገለጽ የመንግስት ኢንስቲቱሽኖችን በዓለም አቀፍ ደረጃም የጥሬ ሀብቶችን ይቆጣጠሩ ዘንድ ግፊት እያደረገ ነው። በዚህ አማካይነትና ራሱን ከማንኛውም የመንግስት ቁጥጥር በማላቀቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ አየር በአየር ንግድን በማስፋፋት ለሰው ልጅ አስፈላጊ የሆኑ የምግብ እህሎችን ሳይቀሩ ወደ ስፔኩሌሽን ኦብጀክትነት በመቀየር የብዙ የሶስተኛውን ዓለም ህዝቦች ዕድል በመወሰን ላይ ነው። ይህ በአንድ በኩል ፣ በሌላ ወገን ደግሞ መንግስታትን በዕዳ ጥገኛ በማድረግና በመተብተብ የፊናንስ ካፒታል ዛሬ በተዘዋዋሪ የብዙ ደካማ አገሮችንና መንግስታትን የኢኮኖሚ ፓሊሲያቸውን ይቆጣጣራል ፤ ወይም ፖሊሲው ለሱ በሚስማማ መልክ እንዲወጣ ጫና ያደርጋል። ይህንን የፊናንስ ካፒታል የበላይነትና በሱ አማካይነት በየጊዜው የሚከሰተውን ቀውስ ለመቆጣጠር ይቻል ዘንድ የመቆጣጠሪያ መሳሪያ(Regulatory Instruments) እንዲወጣ ወይም ግብር እንዲከፍል ከሲቭል ሶሳይቲው ውትወታ ቢደረግም በመንግስትና በፊናንስ ካፒታል መሀከል ባለው መቆላለፍ የተነሳ ፍቱን የሆነ የመቆጣጠሪያ መሳሪያ እስካሁን ድረስ ለማውጣት አልተቻለም። ይህም የሚያሳየው የመንግስቱ መኪና እየደከመ መምጣትና ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ወደ ውጭ ጦርነቶችን ለመቀስቀስና ደካማ አገሮችን ለማመስና ጥሬ-ሀብቶችን ለመቆጣጠር ሽር ጉድ እያለ የመጣበት ሁኔታ ይታያል። ዛሬ በተለይም እንደኮንጎ በመሳሰሉት ከፍተኛ ስትራቴጂክ የሆኑ የጥሬ-ሀብት በሚገኙባቸው አገሮች የሚካሄዱት ጦርነቶች በመሰረቱ በፊናንስ ካፒታልና በስለላ ድርጅቶች የሚደገፉ ናቸው። ብዙ ካፒታሊስት አገሮችና መንግስቶቻቸው በዚህ እርስ በርሱ በሚቃረን የፖለቲካ ሂደት ውስጥ ነው የሚገኙት ማለት ነው። በአንድ በኩል በነሱ አገር የህግ የበላይነት ሰፍኗል ተብሎ ቢሰበክም ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በአፍሪካ ውስጥ የሚካሄደው የእርስ በርስ የወንድማማቾች ጦርነት ከእነሱ ዕውቅ ውጭ እንዳይደለ ብዙ ማስረጃዎችና ዶኩሜንተሪ ፊልሞች ያረጋግጣሉ።

ወደ ኢትዮጵያና ወደተቀሩት የአፍሪካ አገሮች ስንመጣ በአብዛኛዎቹ አገሮች የተቋቋሙት መንግስታትና ኢንስቲቱሽኖቻቸው የኢኮኖሚና የባህል ዕድገታቸው ነፀብራቆች አይደሉም። ከታች ወደላይ ቀስ በቀስ እያሉ ከማቴሪያል ዕድገት ሁኔታዎች ጋር እየታዩና እየተነጻጸሩ አይደለም የተገነቡት። በብዙ የአፍሪካ አገሮች የመንግስት መሰረት ቢኖርም ካፒታሊዝም በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተስፋፋ ሲመጣ መዘርጋት የጀመሩት ቢሮክራሲያዊ መዋቅሮች ከእየአገሮች ፍላጎት አንጻር ሳይሆን ከካፒታሊዝም ፍላጎት አንጻር ነው። የሚሊታሪ ፣ የፀጥታና የሲቪል ቢሮክራሲያዊ መዋቅሮች በየአገሩ ብቅ ብቅ ያለውን የገዢ መደብ ጥቅም የሚያስጠብቁና ሰፊውን ህዝብ ደግሞ መጨቆኛ መሳሪያ በመሆን ሰፋ ያለ ምሁራዊ እንቅስቃሴ እንዳይዳብር አፍነው ለመያዝ ችለዋል። ስለሆነም በአዲሶቹ የህብረተሰብ ኃይሎችና በመንግስት መኪና አማካይነት ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ተቀባይነትን እያገኘ የመጣው ዓለም አቀፋዊ የስራ ክፍፍል ተግባራዊ መሆን ጀመረ። ሁሉም የአፍሪካ አገሮች ጥሬ ሀብት አምራች እንዲሆኑ ተገደዱ። በብዙ የአፍሪካ አገሮች ፣ በተለይም በከተማዎች በከፍተኛ ደረጃ የተስፋፋው የፍጆታ አጠቃቀምና ከውስጥ

የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ ጋር ያልተያያዘው የንግድ እንቅስቃሴ ከበርቴያዊ መደብ ብቅ እንዳይል መንገዱን ሁሉ ሊዘጋበት ቻለ። በመሆኑም ፣ የኢንዱስትሪ አብዮት አካሂዶ ሰፋ ያለ የውስጥ ገበያ ማዳበር በፍጹም የማይቻልበት ሁኔታ ሊፈጠር ቻለ። ከዚህም ባሻገር አንዳንድ የምዕራብ አውሮፓ መንግስታት በአንዳንድ አፍሪካ አገሮች ውስጥ በቀጥታ ጣልቃ መግባትና ኢኮኖሚውን ለነሱ በሚስማማ መልክ እንዲዘጋጅ ማድረግ የአፍሪካ መንግስታትን የምዕራብ አውሮፓና የአሜሪካን ተቀጥያ አድርጓቸዋል። ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ተቀዳሚ ሚና በመጫወት በአንዳንድ አፍሪካ አገሮች ውስጥ ያለውን ቢሮክራሲ በማኮላሸት የመንግስቱ መኪና ማካሄድ የሚገባውን ሁለ-ገብ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንዲሁም የባህላዊ ግንባታ እንዳያካሂድ ሊያግደው ችሏል። የየመንግስታቱ መኪናዎች ለአሜሪካ የጦር አዝማችነት በሚስማማ መልክ በመዋቀራቸውና ውስጠ-ኃይላቸውም ከውጭ በሩቅ የመቆጣጠሪያ መሳሪያ የሚጠመዘዙ ይመስል በየአካባቢው አገሮች ወደ ጦር ቀስቃሽነት እየተቀየሩ በመምጣት ላይ ናቸው። የኢትዮጵያን መንግስት መመልከቱ ብቻ ይበቃል። በዚያው መጠንም አዲሶቹ የገዢ መደቦችና ቢሮክራሲው ራሳቸውን ከህብረተሰቡ እያገለሉ በመምጣት የአገቸውን ጥቅም ከማስጠበቅ ይልቅ በተለይም የአሜሪካንን ጥቅም የሚያስጠብቁ ነው የሚመስለው። ስለሆነም በብዙ የአፍሪካ አገሮች መንግስት የሚባለው መዋቅር ህግን የሚያስከብር ፣ ለህዝብ ደህንነትና ብልጽግናን የሚያመጣ ከመሆን ይልቅ የሚያስፈራራና ድህነትን ፈልፋይ እየሆነ ሊመጣ ችሏል። በተለይም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የተቋቋሙት እንደ አይ ኤም ኤፍና የዓለም ባንክ የመሳሰሉት በየጊዜው በሚያወጡት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች አማካይነት በየአገሮች ውስጥ ድህነትና መዝረክረክ እንዲስፋፋ ሆኗል። ህግና መንግስት ተነጥለው በመታየታቸው ፣ ወይም ደግሞ ሰፊውን ህዝብ የሚካላከለው ኃይል በማጣት ፣ በውጭና በውስጥ ኃይሎች መሀከል በተፈጠረው ያልተቀደሰ ጋብቻ አማካይነት ግለሰብአዊ ነጻነትና ድርጊት ሊታፈኑ በቅተዋል። ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በብዙ የአፍሪካ አገሮች ፣ አገራችንንም ጨምሮ ህግን የሚጥስ ፣ ወይም ደግሞ ለራሱ በሚስማማው መልክ ህግን በማውጣትና ሀብትን ለጥቂቶች በማከፋፋል በሀብታምና በደሀ መሀከል ከፍተኛ ልዩነት እንዲፈጠር የሚያደርግ መንግስታዊ መኪና ተዘርግቷል ማለት ይቻላል ። ይህ የተሰበጣጠረና ለብዙዎች ግልጽ ያልሆነ ሁኔታ ነው ዛሬ ብዙ የአፍሪካ አገሮችን የሚያሸውና በምንስ መልክ ትግሉን ማካሄድ እንደሚቻል የሚያስቸግረው። ከዚህ የተወሳሰበ ሁኔታ በመነሳት የአገራችንን ሁኔታ ደግሞ በመጠኑም ቢሆን እንዳስስ።

ከላይ ቀደም ብሎ የተዘረዘረውን የመንግስት ተግባርና ታሪካዊ ኃላፊነት መሰረት አድርገን በመነሳት ያለፉትን ሁለት መንግስታትና የዛሬውን አገዛዝ ተግባር ስንመረምር ፍልስፍናንና የተፈጥሮን ህግ በመመርኮዝ አልነበረም ኢትየጵያን ሲገዙና ዛሬም ስትገዛ የምትኖረው። በንጉሱ ዘመን ስልጣን ከእግዚአብሔር ለንጉሱና ለወራሾቻቸው አገርን ለመግዛት የተሰጠ ነው ተብሎ ስለታመነበትና ይሰበክም ስለነበር ፣ በሌላ ወገን ግን በአገዛዙ አማካይነት ፣ እኩልነት ፣ በተፈጥሮ ህግ ላይ የተመሰረተ የህግ የበላይነትና ፣ ራሱ መንግስት አገርን በማበልጸግና የያንዳንዱን ዜጋ መብት በማስጠበቅ መውሰድ ስላለበት እርምጃና ኃላፊነት የሚታወቅ አንዳችም ነገር አልነበረም። ስለሆነም በአፄው ዘመን ፣ ራስን በቢሮክራሲያዊ ኃይል ከማጠናከር ህዝቡ መንግስትን እንዲፈራው ከማድረግም ባሻገር በህዝብና በመንግስት መሀከል የሎሌና የገዢ ዐይነት ግኑኝነት ያለ ነበር የሚምስለው እንጂ እያንዳንዱ ዜጋ በእኩልነት የሚታይ ፍጡር አለነበረም። መንግስት አገርን ለማበልጸግ ፣ እያንዳንዱ ዜጋ በችሎታውና ባለው ሀብት ተካፋይ እንዲሆን በማድረግ ህብረተሰቡን ለአጠቃላይ ዕድገት የሚቀሰቅስና ፣ ህብረተሰቡም ዓላማ ኑሮት በስርዓት ወዴት ማምራት እንዳለበት የሚያሳውቅና ራሱም የሚያውቅ አለነበረም። በመሰረቱ የአገዛዙ ጨቋኝነት ከዚህ ህብረተሰቡን በምንና ምን መርሆች ላይ ይዞ መጓዝ እንዳለበትና ፣ አገር ፣ ህብረተሰብአዊና ግለሰብአዊ ነፃነት ምን ማለት እንደሆኑ ካለመገንዘብ የመነጨ ነበር። ዕድገትንና ስልጣኔንም በሚገባ በመረዳት አገራችንን በጸና መሰረት ላይ ለመገንባት ያለው ችሎታ በጣም ውስን ነበር። በመሆኑም ፣ እየተወሳሰበ የመጣውን ዓለም ለመረዳት አለመቻልና ፣ ስትራቴጂያዊ ጥናቶችን የሚያጠኑ ኢንስቲቱሽኖች እንዲዘረጉ ባለመደረጋቸውምና ዝም ብሎ በጭፍን የፊዩዳላዊ አስተሳሰብ ብቻ መመራቱ የአገራችንን ዕድገት ሊቀጨው ችሏል። በአፄው ዘመን የተዘረጋው ስርዓት ኢትዮጵያን ለጠላት አጋልጦ ሂዷል ማለት ይቻላል።

የወታደሩም አገዛዝ ከዚህ ዐይነቱ አስተሳሰብና የአኗኗር ኖርም እንዲሁም ስርዓት የፈለቀ እንደመሆኑ መጠን የፈለገውን ያህል የሶሻሊዝምን ካባ ለብሻለሁ ቢልም ይወስዳቸው የነበሩ እርምጃዎች በሙሉ እየታሰቡና ፣ አገርን ለመገንባትና እኩልነትን ለማስፈን ደረጃ በደራጃ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች በማጤን አልነበረም አገርን ይገዛ የነበረው። የወታደሩን አገዛዝ ልዩ የሚያደርገው ፣ በአንድ በኩል ህዝቡን ሊጠቅሙ የሚችሉ እርምጃዎችን ቢወስድም ፣ በሌላ ወገን ደግሞ እዚያው በዚያው አመጽንና ጉልበትን ያስፋፋና ፣ ሺህ በሺህ የሚቆጠሩ ካድሬዎችን በማፍራት ጋጠ-ወጥነትን በማስፋፋት ህዝቡ በፍርሃት ዓለም ውስጥ እንዲኖር ማድረጉ ነው። ይሁንና ይህ አገዛዝ በዘረፋ የሚታወቅ አለነበረም ፤ ወይም ደግሞ የወንበዴዎች አገዛዝ ነው ብሎ መናገር በፍጹም አይቻልም።

ወደ ዛሬው አገዛዝ ስንመጣ ነው ሁሉ ነገር ግራ የሚገባን። የዛሬው አገዛዝ በአነሳሱ ኢትዮጵያዊ ኃይል ነኝ ብሎ የሚያምን አልነበረም። ራሱን ከሌላው ነጥሎ ያየና ዛሬም የሚያይ ፣ ጠቅላላው የኢትዮጵያ ህዝብ ይጠላኛል ወይም ይንቀኛል ብሎ የሚገምትና ፣ እንጀራ እናት በድላ ያሳደገችው ልጅ ይመስል እያደገ ሲሄድ ቂጭቱን ለመወጣት የሚጠባበቅ የሚመስል ፣ እርቆ አስተዋይነትና አሳቢነት በጎደለው መልክ የቂም በቀል ፖለቲካ ማካሄድ ጀመረ። በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዐመታት ከሻቢያ ጋር በማበር የተካሄደው አጠቃላይ ዘረፋ ፣ ቀጥሎ ደግሞ ከፋፍሎ ለመግዛት እንዲያመች ተግባራዊ መሆን የጀመረው የክልል ፖለቲካ የሚያሳየው ፣ ይህ አገዛዝ ተቀባይነት ያለውና ህጋዊ መንግስት ሳይሆን ስልጣንን ተገንና መሳሪያ በማድረግ የራሱንም ህግ ሳይቀር እንኳ በመርገጥ ወደ ተራ ዘራፊነት እያመራ እየመጣ መሆኑን ነው የሚያረጋግጠው ። ለዘረፋ ፖለቲካው የአሜሪካ ጉያ ስር መውደቁና ቡራኬ ማግኘቱ ፣ በኒዎ-ሊበራሊዝም ላይ የተመረኮዘውን የመዋቅር ማስተካከያ(Structural Adjustment Program) የሚባለውን ፣ ብልጽግናን ሳይሆን ድህነትን ፈልፋይ የሆነውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረጉ ራሱን አግሎ እንዲወጣ አድርጎታል። በዚህ የዘረፋው ፖለቲካው እንዲገፋበትና ህዝባችንን በማቴሪያል ሁኔታው ብቻ ሳይሆን ከህሊና አንጻርም መንፈሱ እንዲዳሽቅ ማድረግና በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ፊት አቅመቢስነቱን በማረጋገጥ ወደ ለማኝነት እንዲወረወር ማድረግ ፣ በአጠቃላይ ሰለጥንኩኝ የሚለው የምዕራቡ ዓለም በዚህ ዐይነቱ ኢትዮጵያን በማዳከሙና ህዝባችንን በማደኸየት ፖለቲካው በድብቅም ይሁን በግልጽ ረድቶታል። በእንደዚህ ዐይነት በተቀነባበረ ሴራና ድጋፍ ብቻ ነው ይህ አገዛዝ እየጠነከረና አገርን ወደ መሸንሸንና ወደ መሸጥ እያመራ የመጣው። ለውጭ „እንቬስተሮች“ የሚሰጠው ብዙ ጋሻ መሬት የዚህ የዘረፋው ፖለቲካው አንድ አካል ነው። በራሱ ህገ-መንግስትም እንኳ መሬትን መሸጥና መለወጥ የተከለከለ ቢሆንም በመቸብቸብ ድርጊቱ እየገፋበት ነው። ስለሆነም ህግና ስርዓት ምን እንደሆኑ ሰለማይረዳና ህዝባችንን ከእንስሳ በታች በመቁጠር በማን አለብኝነት ህዝብን ያፈናቅላል ፤ የአገርን መሬት ይቸበችባል። የሺህ ዐመት ራስ ምታት እየሰጠን ነው ማለት ነው። አሁን ደግሞ ለመጨረሻ ጊዜ ኢትዮጵያን ወደ ፓኪስታንነት ለመለወጥ ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የሰው-አልባ አውሮፕላን ማረፊያና ከዚያ ተነስቶ ሽብርተኞች የሚላቸውን እንዲደበድብ የፈቀደለት የጦር ካምፕ የቱን ያህል የዚህን አገዛዝ ህገ-አልባነት የሚያረጋግጥ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። የተቃዋሚ ኃይሎችም ዕውነተኛ የነፃነት ትግል ማድረጋቸውና አለማድረጋቸው የሚለካው በዚህ ላይ በሚወስዱት አቋማቸው ነው። ስለሆነም ትግላችን ውስብስብ እየሆነ በመምጣት የትኛው ኃይል ለዕውነተኛው ብሔራዊ ነፃነትና ለኢኮኖሚ ዕድገት እንደሚታገል ለማወቅ ግራ የተጋባንበት ጊዜ ነው። የወደፊቱም ትግልም በተራ የሊበራሊዝም መርሆች ላይ የተመሰረተ ትግል ወይስ ለዕውነተኛ ህዝባዊ ነፃነት በሚለው ላይ የሚያተኩር ይሆናል ማለት ነው።

ያም ሆነ ይህ የፖፕ ቤኔዲክት 16ኛን አባባል ለማስመር የዛሬው አጋዛዝ ዘራፊያዊ አገዛዝ ተብሎ ከመጠራት በስተቀር ሌላ ስም ሊሰጠው ከቶም አይገባም። የህዝባችን በረሀብና በድህነት መሰቃይት ፣ በዋጋ መናር የተነሳ አስፈላጊ ነገሮችን ገዝቶ ለመመገብ አለመቻል ፣ የከተማዎች መዝረክረክና በስነ-ስርዓት ለመስራት አለመቻል ፣ ወይም ምንም ዕቅድ አለመኖር ፣ የህዝባችን ተስፋ መቁረጥና ህሊናው መሰበር የሚያረጋግጠው የኢህአዴግ አገዛዝ ምንም ዐይነት ህዝባዊና ብሔራዊ ባህርይ እንደሌለው ነው። በ1338

ዓ.ም አምብሮጊዮ ሎሬንዜቲ የሚባለው ጣሊያዊ ምሁር ፣ Allegory of Good and Bad Government በሚለው መጽሀፉ ውስጥ ፣ ጥሩ አገዛዝ በቆንጆ ህንጻዎች ፣ በሚያማምሩ ሱቆችና ፣ ህዝቡን በሚያስደስቱ በልዩ ልዩ ነገሮች ሲገለጽ ፣ መጥፎ አገዛዝ ደግሞ አገርን በማፈራረስ ፣ በመሰረር ፣ በዝርፊያና በግድያ የሚገለጽ ነው ይላል። ዛሬ በአገራችን ያለው ሁኔታ ይህንን የዛሬ ስምንት መቶ ዐመት ገደማ በአምብሮጊዮ ሎሬንዜቲ የተገለጸውን አባባል ነው የሚያረጋግጥልን።

**ፈቃዱ በቀለ**

fekadubekele@gmx.de